# ሥነ - ጥበባት ትምህርት

## የተማሪዎች መጽሐፍ











## 3ኛ ክፍል

## ይህንን መጽሐፍ በጥንቃቄ በመያዝ ተጠቀምበት/ሚበት




ይህ መጽሐፍ የትምህርት ቤትህ/ሽ ንብረት ነው፡፡ ጉዳት እንዳታደርስበት/ሺበት ወይም ጉዳት እንዳይደርስበት ጠብቅ/ጠብቂ፡፡

ይህን መጽሐፍ በጥንቃቄ በመያዝ መከተል ያለበትን መመሪያዎች ተጠቀም/ሚ

1. መጽሐፉን በጋዜጣ፣ በፕሊስቲክ ወይም በተገኘው ወረቀት ሸፍን/ኚ ፡፡
2. መጽሐፉን ሁሌጊዜ ደረቅ እና ንፁህ በሆነ ቦታ አስቀምጥ/ጪ፡፡
3. መጽሐፉን ሁሌጊዜ በንፁህ እጅ ያዝ/ዢ፡፡
4. መጽሐፉን ላይ ምንም አይነት ፅሁፍ አትፃፍ/ፊ፡፡
5. የምትፈልገውን/ጊውን ቦታ በመክፈት ካርድ ወይም ብጣሽ ወረቀት እንደ ምልክት በማስቀመጥ ተጠቀም/ሚ ፡፡
6. አንድም ገፅ ወይም አንድም ስዕል ከውስጡ ለመቅደድ አትሞክር/ሪ፡፡
7. የተቀደደ ገፅ ካለ በማስትሽ ወይም በፕሊስተር አያይዝ/ዢ፡፡
8. በመንገድ ላይም መጽሐፍ በማይጎዳ ሁኔታ ያዝ/ዢ፡፡
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታውስ/ሺ በጥንቃቄ ይሁን፡፡
10. በአዲስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትጠቀም/ሚ፣ መጽሐፉን በጀርባ በማስቀመጥ በአንድ ጊዜ ጥቂት ገፆችን ብቻ ገልብጥ/ጪ፡፡ ቀስ ብለህ/ሽ የመጽሐፉን መሃል በእጅህ/ሽ ጫን በል/ይ፡፡ ይህም ዘዴ የመጽሐፉን ሽፋን እንዳይጎዳ ይረዳል፡፡

# የሥነ - ጥበባት ትምህርት
# የተማሪው መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል


**አፋን ኦሮሞ አዘጋጆች**

ደሜ ቶሊና

ሉባባ ጀማል

ታደሰ ድንቄ

**አፋን ኦሮሞ ኤዲተሮች**

ደንደአ ቦጋለ

ከበቡሽ ለሜሳ

ለሚ ቤኛ

**በአፋን ኦሮሞ ገምጋሚዎች**

ድርባ ማሞ

ደቀቦ ጉዬ

እስማኤል ሐሰን

**ተርጓሚ**

ሙሉቀን አብራሐም

**ኤዲተር**

ደቀቦ ጉዬ

**ግራፊክስ**

ታደሰ ድንቄ

**ገላጭ ስዕል**

ቡዛዮ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2022

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2022 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝቶ ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

# መውጫ


የሥነ-ጥበባት ግንዛቤዎች........................................................................1

**ምዕራፍ 1**........................................................................1

1. የስነ-ጥበባት አይነቶች መለያ........................................................................1

1.1 የሙዚቃ ኖታዎች........................................................................1

**1.3.ፎቶ የማንሳት ዘዴ እና የዲራማ ጫወታዎች**........................................21

**ምዕራፍ 2**........................................................................27

የፈጠራ ችሎታ........................................................................27

**2.1 የሙዚቃ ድምፆች፣ኖታዎች እና የሙዚቃ መሣርያ ምት**........................27

**2.2 ቀላል የሆኑ ቅርፆችን ቀለም መቀባት**........................................36

**2.3. የመሠረታዊ ቀለማት ድብልቅ እና ቀጥተኛ ህትመት**........................46

**2.4 የዲራማ ፣ቪድዮ እና ፎቶ መልዕክቶች**........................................55

**ምዕራፍ 3**........................................................................62

የባሕል እና ታሪክ_ተጨባጭ ሁኔታ ...............Error! Bookmark not defined.

3. የባሕል ዕሴት መግለጫ........................................................................62

**3.1 ባሕላዊ እና ዘመናዊ የሥነ-ጥበብ ሥራዎች**........................................62

3.2 የባሕላዊ እና ዘመናዊ መዚቃ ታሪክ........................................................81

**3.3 የትያትር ከንዉን እሴቶች መገለጫ**................................................84

**የሥነ ጥበባት**........................................................................91

**መሥዕብ**........................................................................91

**ምዕራፍ 4**........................................................................91

4 የሥነ ጥበባት ሥራዎች አድናቆት................................................................91

4.1 የስነ ጥበብ አድናቆት....................................................................91

4.2 የባሕላዊ ሙዚቃ አድናቆት....................................................................100

ምዕራፍ 5....................................................................................105

5.1 የስነ-ጥበባት ግኑኝነት....................................................................105

5.2 ሌሎች ትምህርቶችን መማር ውስጥ ያለዉ የሥነ- ጥበባት ጥቅሞች.107

# ምዕራፍ 1

# የሥነ-ጥበባት ግንዛቤዎች

## 1. የስነ-ጥበባት አይነቶችን መለየትና መግለፅ

### 1.1 የሙዚቃ ኖታዎች

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ሩብ ኖታ በማንበብ ትጫወታላችሁ፡፡
- የሩብ ኖታ ቅርጽ በመሳል ታሳያላችሁ፡፡
- በሩብ ኖታ የተፃፉ ቀላል ምቶችን በማንበብና በመጫወት ትደሰታላችሁ፡፡
- የባህላዊ ሙዚቃ ታሪክ ትረዳላችሁ፡፡
- የተለያዩ መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ፡፡

# መግቢያ

ሙዚቃ አለም አቀፋዊ ቋንቋ ነው። ሳይንሳዊ በሆነ መልክ ስለ ሙዚቃ ታውቁ ዘንድ ቀመሩን ባለፈው ትምህርት መማር ጀምራችኋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ኖታዎችን፣የባህላዊ ሙዚቃ ታሪክ፣ መዝሙርና ባህላዊ ውዝዋዜዎችን ትማራላችሁ፡፡

## 1.1.1 ሩብ ኖታ

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ሙሉ ኖታ አና ግማሽ ኖታ ምን ይመስላሉ ?
2. እያንዳንዱ ኖታ ስንት የምት ዋጋ አለው?
3. ሙሉ ኖታ እና ግማሽ ኖታ እንዴት እንጫወታለን?

ሩብ ኖታ እንደ ለሎች ኖታዎች የሙዚቃ ፊደል ሆኖ አንድ የምት ዋጋ ያለዉ ነው፡፡ ምልክቱም ወይም ቅርፁ ከግማሽ ኖታ ጋር የሚመሳሰል ሆኖ፣ ከራስ ላይ የተቀባ ነው፡፡

**የሩብ ኖታ ቅርፅ**



## ተግባር

1. ሶስት የሩብ ኖታን ምልክት  በመሳል አሳዩ፡፡
2. የሩብ ኖታ ምት ዋጋ ስንት ነው?
3. ሩብ ኖታ እንዴት መጫወት እንችላለን? አሳዩ ፡፡


## ሩብ ኖታን ማንበብ

ሩብ ኖታ አንድ የምት ዋጋ አለዉ፡፡ ስለዚህ እጃችንን አንድ ጊዜ አጨብጭበን “ta..” ብለን እንጫወታለን፡፡

ለምሳሌ:








እጃችንን እያጨበጨብን  ሩብ ኖታ በማንበብ መጫወት፡፡




1.



2.





3.




ሩብ እና ግማሽ ኖታ በማደባለቅ ማንበብ እና መጫወት፡፡


1.







2. 






3. 



4. 




5. 

6. 



## 1.1.2 ሩብ ዕረፍት

### የግንዛቤ ጥያቄዎች


1. ሩብ ዕረፍት ምን እንደሚመስል ታስታውሳላችሁ?
2. የሩብ ዕረፍት ምልክት በመሳል፣ እንዴት እንደሚነበብ እና እንደምንጫወት ለጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡

የሩብ ዕረፍት ከሩብ ኖታ ጋር እኩል አንድ የምት ዋጋ አለዉ፡፡ ልዩነቱ ድምፅ መኖሩና አለመኖሩ ነው፡፡ ሩብ ኖታ ስንጫወት ድምፅ አለዉ፤ ነገር ግን ሩብ ዕረፍት ስንጫወት ድምፅ ሳናሰማ እንጫወታለን፡፡

ከዚህ በታች ያለውን የሩብ እረፍት ቅርፅ በማየት ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ምልክቱን በመሳል አሳዩ፡፡




ሩብ እረፍትን በማንበብ ተጫወቱ፡፡





# የሙዚቃ ኖታዎች የአነባብ ልምምድ

**ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች፣ ዕረፍት ባለበት ቦታ ዝም በማለት፣ ድምፅ ያላቸዉ ኖታዎች ደግሞ “Taa” የሚል ድምፅ በማሰማት እጅ በማጨብጨብ የምት ዋጋ እየቆጠራችሁ ተጫወቱ፡፡**










1. 

2. 




1. 









## 1.2 መሠረታዊ ቀለማት

**ተግባር**


የአዕዋፋት፣ የቤት እንስሳቶች፣ የዱር እንስሳቶችና በአከባቢያችን የሚገኙ አበባዎች መልክ ምን እንደሚመስሉ በቡድን ከተወያያችሁት በኋላ ቀለማቸውን ለመምህራችሁ ግለፁ፡፡

በአንደኛና በሁለተኛ ክፍል ቀለም የመቀባት ተግባራትን እንደተለማመዳችሁ ይታወቃል፡፡ በዚህ የትምህርት ርዕስ ስር ደግሞ የመሰረታዊ በለማት አይነቶችን ትማራላችሁ፡፡ .

መሰረታዊ ቀለም የሚባሉት ቀይ ቢጫና ሰማያዊ ቀለማት ናቸው፡፡ እነርሱም ለሌሎች ቀለማት ሁሉ መሰረት ናቸው፡፡. እነዚህን ቀለማት መግኘት የምንቸለው ከተፈጥሮ ስለሆነ እንደ ሌሎች የቀለም አይነቶች በመደባለቅ ማግኘት አንችልም፡፡

ተፈጠሯዊ ቀለማት ለምሳሌ የአዕዋፋት፤የቤት እንስሳቶች፤የዱር እንስሳቶችና በአከባቢያችን የሚገኙ አበባዎችና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

# የሚከተሉትን ምሳሌዎች ተመልከቱ



በአከባቢያችን የሚገኙ ተፈጥሮአዊ ነገሮች ያላቸዉ ቀለማት

እነዚህ የተለያዩ ተፈጥሯዊ ውበቶችን ሥዕል ሥለው ለማሳየት፣ ለቅብ የሚውሉ መሠረታዊ ቀለማትን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

የሰው ልጅ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ዋሻ ውስጥ ሲኖር፣ ሃሳቡን ሲገልፅ ከነበረባቸው መንገዶች አንዱ በቀለም ቅብ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች/ታሪክ ያመለክታል፡፡

## 1.2.1 የመሠረታዊ ቀለም አይነቶች

**ተግባር 2**

1. መሠረታዊ ቀለሞች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
2. በአከባቢያችሁ ከሚገኙ ሦስት ነገሮች በመጥቀስ፣ መልካቸውን/ቀለማቸውን ለመምህራችሁ ግለፁ፡፡

ቀለም እይታ ወይም ግንዛቤ ነው፡፡ ስለዚህ በአከባቢያችን የምናያቸው ነገሮች ሁሉም የተለያዩ ቀለም/መልክ አላቸው፡፡

ለምሳሌ የአደይ አበባ ቢጫ ብለን እንጠራለን፡፡ እንዲሁም እንስሳቶችና የተለያየ መልክ ያላቸው አዕዋፋትን ቀይ፣ ሰማያዊ፣ ጥቁር እና የመሳሰሉትን ብለን መጥራት እንችላለን፡፡

ስለዚህ፣ቀለም የአንድን ነገር መልክ ነው፡፡ የቀለማትን መልክ በአይን አይተን ሥማቸውን መለየት እንድንችል የሚያደርግ፣

የፀሐይ ብርሃን ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የፀሐይ ብርሃን ቀለማትን በየመልካቸው እንድንለይ ይረዳናል፡፡


መሠረታዊ ቀለሞች ለሁሉም ቀለሞች መሠረት ናቸው፡፡ መሠረታዊ ቀለሞች እንደ ሌሎች ቀለሞች በመቀየጥ ማግኘት አንችልም፤ ነገር ግን እርስበርሳቸው በመቀየጥ ሌሎችን ቀለሞችን ማግኘት እንችላለን፡፡ እነዚህም ቀለሞች የአንደኛ ደረጃ (ሰው ሰራሽ መሠረታዊ ቀለም) በመባል ይጠራሉ፡፡




ሦስት መሰረታዊ ቀለሞች አሉ እነዚህም፡-

- ✓ ቀይ
- ✓ ቢጫ
- ✓ ሠማያዊ ናቸዉ፡፡

ከሦስቱም መሠረታዊ ቀለማት እኩል መጠን በመውሰድ እንድ ላይ ብናደባልቅ ግራጫ መልክ ይሰጠናል፡፡



ይህም ማለት፡

ቀይ +ቢጫ + ሠማያዊ = ግራጫ/ ድፍርስ ቀለም ይሰጠናል፡፡

## ልምምድ 1


**ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች ተራ በተራ፣ ለቀለም ቅብ ባዘጋጃችሁት ወረቀት ላይ ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀቡ፡፡**







## ልምምድ 2

ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች ተራ በተራ፤ለቀለም ቅብ ባዘጋጃችሁት ወረቀት ላይ ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀቡ፡፡




## ልምምድ 3

**ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች ተራ በተራ፤ለቀለም ቅብ ባዘጋጃችሁት ወረቀት ላይ ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀቡ፡፡**




**ልምምድ 4**. ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች ተራ በተራ፤ ለቀለም ቅብ ባዘጋጃችሁት ወረቀት ላይ ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀቡ፡፡



## ልምምድ 5

**ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች ተራ በተራ፤ለቀለም ቅብ ባዘጋጃችሁት ወረቀት ላይ ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀቡ፡፡**



# 1.3. ፎቶ ማንሳትና ድራማ መጫወት





## ፎቶ ማንሳት



ኢች ዲ ካሜራ



ትራይፖድ (የካሜራ ማስቀመጫ)



ፎቶግራፍ ለማንሳት ካሜራ የያዘች ልጅ

# በካሜራ የተነሱ ፎቶዎች

## ልምምድ 1

1. ካሜራ ወይም ስልክ በመጠቀም ከጓደኞቻችሁ ጋር ፎቶ ተነሳሱ.

ፎቶ ከሥነ ጥበባት ውስጥ አንዱ ሲሆን፤ ህይወት ያላቸው እና የሌላቸውን ነገሮችን ፊትለፊት በማድረግ በካሜራ መቅረፅ ነው፡፡ ፎቶ ለመቅረፅ የሚረዳን መሳሪያ ደግሞ ካሜራ ይባላል፡፡ ፎቶ መነሳት የሚችሉ ነገሮች ሰው፣እንስሳት እፀዋት

ድንጋይ ውሀ ሰማይ በአጠቃላይ በዚህ ምድር ላይ የሚታዩ ነገሮች ሁሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡በእንቅስቃሴ ላይ ያሉ





ነገሮችንም ፎቶ ማንሳት ይቻላል፡፡





ፎቶግራፍ ከስዕል የሚለየው ካሜራን በመጠቀም የተፈለገውን ነገር እንዳለ ምንም ለውጥ ሳይደረግበት የሚወሰድ ነው፡፡ ስዕል ደግሞ የነገሮችን ምስል አስመስሎ ማንሳት በሚችል ሰው በወረቀት፣ በጨርቅ እና በተለያዩ ነገሮች ላይ በእጅ የሚሰራ ነው፡፡

## ፎቶ እና ድራማ

ፎቶ ማንሳት በሚል ርዕስ ስር ባለፈው ትምህርት ሰዎችን ወይም እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ነገሮችን ፎቶ ማንሳት እንደሚቻል ተምራችኋል፡፡ እንዲሁም የትያትር ጨዋታን ወይም ድራማ የሚሰሩ ሰዎች ድርጊታቸውንና ስሜታቸውን ፎቶ በማንሳት መግለፅ ይቻላል፡፡







*በካሜራ የተቀረፁ የድራማ ጭውውት የሚያሳዩ ፎቶዎች፡፡*

## ልምምድ 2

## የምታውቁትን አንድ ቀላል ድራማ በመድረክ ላይእየተጫወታችሁ በየተራ እርስ በእርሳችሁ ፎቶ እየተነሳሳችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ

## መልመጃ 1

## የሚከተሉትን ጥያቄዎችን በተጠየቃችሁ መሠረት መልሱ፡፡

1. ፎቶ እና ሥዕል ልዩነት የላቸውም፡፡

   ሀ. እዉነት ለ. ሐሰት

2. ከሚከተሉት ፎቶ መነሳት የሚችለው የቱ ነው ?

   ሀ. ሰው ሐ. እንስሳት

   ለ. እፅዋት መ. ሁሉም መልስ ናቸዉ፡፡

3. የተክኖሎጂ መሣርያ ሆኖ ፎቶ ለማንሳት የሚያገለግል---------------------ይባላል፡፡

## ተግባር 4

1. የጓደኞቻችሁን ወይም የቤተሰቦቻቸውን ፎቶ በማምጣት ለክፍል መምህራችሁ አሳዩ !

# ምዕራፍ 2

# የፈጠራ ችሎታ

## የስነ-ጥበባት ልምምድ

## 2.1. የሙዚቃ ድምፆች፣ ኖታዎች እና የሙዚቃ ምት መሣሪያዎች

### 2.1.1 የሙዚቃ ድምፆች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመወያየት መልሱ፡፡

1. ከሙዚቃ ድምፆች የትኞቹን ታውቃላችሁ? የራሳችሁን ምሳሌ ስጡ፡፡
2. ወፎች ሲያዜሙ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እንዴት ያዜማሉ?
3. ሰዎች የሙዚቃ መሣሪያዎችን ሲጫወቱ አይታችሁ ታውቃላችሁ? የሰማችሁትን የሙዚቃ መሳሪያዎች ድምፅ አስመስላችሁ አሰሙ?

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የሰው ልጅ፣ በድምፁ መዘመርና የተለያዩ ባሕላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን መጠቀም ጀመረ፡፡

አሁን ደግሞ በዘመናዊ መልክ የምንጠቀምባቸው ፤ ሰባት (7) የሙዚቃ ድምፆች አሉ፡፡ እነሱም፡

“Doo Ree Mii Faa Sool Laa Sii Doo” ናቸው ፡፡

እነዚህንም ድምፆች በፒያኖ ወይም በኪቦርድ ላይ መስማት ይቻላል፡፡



Doo Ree Mii Faa Sool Laa Sii Doo




## 2.1.2 የሙዚቃ ኖታዎች

በሚከተሉትን ጥያቄዎች ላይ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች ግለፁ፡፡


1. ኖታ ምንድነው?
2. ኖታ ለምን ይጠቅማል?
3. ምን አይነት ኖታዎችን ታውቃላችሁ?

ኖታ የሙዚቃ ፊደል ፤ምት እና ዜማ የሚጻፍበት መሆኑን ተምራችኋል፡፡ የተለያዩ ኖታዎች አሉ እነዚህም፡-


1.**ሙሉ ኖታ፡** ክብ የሚመስል እና የምት ዋጋው አራት (4) ነው፡፡ ቅርጹም የሚከተለውን ይመስላል፡፡



2. **ግማሽ ኖታ፡** ሙሉ ኖታ የሚመስል ሆኖ፣ ከራስ ላይ አጭር ግንድ ያለውና ያልተቀባ ሲሆን የምት ዋጋው ሁለት (2) ነው፡፡ ቅርጹ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡፡



3. **ሩብ ኖታ፡** ደግሞ ግማሽ ኖታ የሚመስል ሆኖ፤ራሱ የተቀባ ሲሆን የምት ዋጋዉ አንድ ነው፡፡





## 2.1.3 እረፍት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከጓደኞቻችሁ ጋር በመስራት ለክፍል ተማሪዎች አብራሩ፡፡

1. የኖታ እረፍት የሚባለው ምንድነው?
2. የኖታ እረፍት ለምን ይጠቅማል?
3. ምን አይነት የኖታ እረፍቶችን ታውቃላችሁ?

እረፍት የሙዚቃ ፊደል የሆነ፣ በምትና ዜማዎች ውስጥ ዋጋቸው የሚተመንበት ቦታ በዝምታ የሚታለፍ ነው፡፡

የተለያዩ የእረፍት አይነቶች አሉ እነርሱም፡-

1. **ሙሉ እረፍት፡** የቆይታ ምት ዋጋ አራት (4) ያለውና፣ቅርጹ የሚከተለውን ይመስላል፡፡



2. **ግማሽ እረፍት፡** የቆይታ ምት ዋጋ ሁለት  ያለውና፣ቅርጹ የሚከተለውን ይመስላል፡፡



3. **ሩብ እረፍት፡** የቆይታ ምት ዋጋ አንድ  ያለውና፣ ቅርጹ የሚከተለዉን ይመስላል፡፡




## ተግባር

ከዚህ በታች የተጻፉት ኖታዎችን መጀመርያ በግል ከተለማመዳችሁ በኃላ፤በቡድን እጅ በማጨብጨብ ወይም ከበሮ በመምታት አብራችሁ ተጫወቱ፡፡

1.







2. 






3. 

4. 



5.



## 2.1.4 የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች

### ተግባር

1. በአከባቢያችሁ የሚገኙ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች ፃፉ፡፡
2. የጻፋችሁት የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች መቼ እና እንዴት እንደሚጫወት አሳዩ፡፡
3. በአከባቢያችሁ የሚገኙ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች ሥዕል በመሣል ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ባሕላዊ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን በተለያየ ጊዜ መጠቀም እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፡

- በበዓል ጊዜ
- የሠርግ ጊዜ
- በቤተ እምነት ተቋማት ውስጥ
- መዝናናት በምንፈልግበት ጊዜ
- ለተለያዩ ለባሕላዊ ጉዳዮች እና ወዘተ.....ናቸው፡፡

## የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች አይነት

ባሕላዊ እና ዘመናዊ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች በመባል ለሁለት ይከፈላሉ፡፡

1. ባሕላዊ እና ዘመናዊ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች

ከባሕላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ታዋቂ የሆኑ ከበሮ፣መረካሸ፣መምቻ (ካባላ) እና ወዘተ...ናቸው፡፡

### ሀ.ከበሮ

ከቆዳ እና እንጨት ልሰራ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሰዎች እንደተመቻቸው በተለያዩ ቅርጽ ይሰራሉ፡፡



ከበሮ በእጅ ወይም በሁለት መምቻ ዱላ እንጫወታለን፡፡

የክፍል ሥራ

1. በአከባቢያችሁ ከበሮ ከምን ይሠራል?

## ለ. ጽናጽል

ጽናጽል እብዛኛዉ ጊዜ በቤተ እምነት ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡ ነገር ግን በሚወዛወዝ ጊዜ የሚያሰማ የምት ድምፅ፤ለዘመናዊ ሙዚቃ አስፈላጊ ነው፡፡

ጽናጽል ከብረት፣እንጨት እና ቆርኪ የሚሠራ ሲሆን፤በማወዛወዝ እንጫወታለን፡፡





ሥዕለል 2 ጽናጽል

## ሐ. መረከሽ

መረከሽ ደግሞ ቅል በማድረቅ ፣ጠጠር በውስጡ በመጨመር እና በማወዛወዝ በሚያሰማ የምት ድምፅ የምንጠቀምበት ነው፡፡


መረከሽና ጽናጽል የሚያወጡት ድምጽ በጣም የሚቀራረብ ነው፡፡ የሁለቱም ድምፅ (ካሽ፣ካሽ፣ካሽ) የሚል ነው፡፡



ሥዕል 2 ሐ መረከሽ

መ. **መምቻ (ከበላ)**

ከባሕላዊ ሙዚቃ መሣሪያ አንዱ ሲሆን፣በሁለት እጅ ይዘን በመምታት እንጫወታለን፡፡ መምቻ ከጠፍጣፋ እንጨት ይሠራል፡፡



መምቻ (ከበላ)

## 2.2. ቀላል የሆኑ ቅርፆችን ቀለም መቀባት

### 2.2.1. ቀላል ቅርፃቅርፅ መንደፍ

ባለፈው ክፍል የተለያዩ መስመሮችን በማገጣጠም ቀላል የሆኑ የቅርጽ ንድፍ መንደፍና ቀለም መቀባት መለማመዳችሁ ይታወቃል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ቀላል የሆኑ ቅርፅ እና

ገፅ/ፎርሞችን በመሳል ቀለም እንዴት እንደሚቀባ መለማመድ ትማራላችሁ፡፡


## ተግባር

1. የአዕዋፋት ቅርፅ፣ እንስሳቶች እና የተለያዩ አበባዎች ንድፍ መንደፍ ፣ቀለም መቀባት የእርስበርሳችሁን ሥራ በማየት አድንቁ! ጠንካራ እና ደካማ ጎን በመለየት፣

ቀላል የሆኑ ቅርጾችን ቀለም መቀባት ማለት፣የተፈጥሮ ሆነ ሠው ሰራሽ ነገሮች ያላቸውን ቅርጽ በማየት ንድፍ ከነደፉችሁ በኋላ፣ እንደየመልኩ በቀለም ማስዋብ ነው፡፡


## ልምምድ 1

የሚከተሉትን ቀላል ቅርፃ ቅርፆች በመደጋገም በመንደፍ ተለማመዱ፡፡




## 2.2.2. የቀላል ፎርም ንደፍ መስራት

ፎርም ማለት የተወሰኑ መስመሮችን በመያያዝ የሚሠራ ሲሆን ቁመት፣ ርዝመትና ስፋት ያለው ነው፡፡ ለምሳሌ በካሬ (ስኩዌር) ላይ ሰያፍ መስመር በመጨመር ኪዩብ፣ እና በሶስት ጎን ላይ ሞላላ መስመር በመጨመር የኮን ፎርም መፍጠር ይቻላል፡፡ እንደዚሁም በክብ ላይ ብርሃንና ጥላ በማድረግ እስፈር መስራት ይቻላል፡፡



## ልምምድ 2


ከዚህ በታች ያሉትን ፎርሞች ደጋግማችሁ ንድፋቸውን በመስራት ተለማማዱ፡፡



## 2.2.3. ቀላል የሆኑ ቅርፃ ቅርፆችና ፎርሞችን ቀለም መቀባት


ቅርፆችና ፎርሞችን ቀለም መቀባት ማለት በመስመር ንድፋቸው የተሠሩትን ቀለም መቀባት ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፡




## ልምምድ 3


ቀጥሎ የተሰጠውን ቅርፅ በደብተራችሁ ውስጥ ንድፉን ከሰራችሁ በኋላ ቀለም ቀቡ፡፡



## ልምምድ 4

ሀ. ቀጥሎ የተሰጠውን ቅርፅ በደብተራችሁ ውስጥ ንድፉን ከሰራችሁ በኋላ ቀለም ቀቡ፡፡






## ልምምድ 5

**ሀ. የሚከተሉትን ስዕሎች ደብተራችሁ ላይ ንድፉን ካስቀመጣችሁ በኋላ ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ ቀለም ቀቡ፡፡**












ለ. የሚከተሉትን ስዕሎች ደብተራችሁ ላይ ንድፉን ካስቀመጣችሁ በኋላ ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ ቀለም ቀቡ፡፡





## ልምምድ 6

ከዚህ በታች ያሉት ሥዕሎችን ቅድምተከተሉን በመጠበቅ ለቀለም ቅብ ባዘጋጃችሁት ወረቀት ላይ ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀቡ፡፡



## መልመጃ 4.

ከዚህ በታች ያሉትን ከደረት በላይ ሥዕል ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ፤ለቀለም ቅብ ባዘጋጃችሁት ወረቀት ላይ ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀቡ፡፡

# 2.3. የመሠረታዊ ቀለማት ድብልቅ እና ቀጥተኛ ህትመት

## 2.3.1 የመሠረታዊ ቀለማት ድብልቅ

### የግንዛቤ ጥያቄ

### ቀለም ማደባለቅ ማለት ምን ማለት ነው?


በሺዎች የሚቆጠሩ እና የተለያዩ መልክ ያላቸዉ ነገሮች በአከባቢያችን እንደሚገኙ በምዕራፍ አንድ ተምራችኋል፡፡ የቀለም ድብልቅ ማለት የተለያዩ አይነት ቀለማትን እኩል በሆነ ወይም ባልሆነ መጠን መደባለቅ ነው፡፡

ለቀለም ቅብ የሚያገለግሉ ሦስቱ መሠረታዊ ቀለማትን በመደባለቅ የተለየ ቀለም መፍጠር ይቻላል፡፡ እነዚህን መሠረታዊ ቀለማት በአንደኛ ምዕራፍ ውስጥ ተምራችኋል፡፡

ሁለት የመሠረታዊ ቀለማት ተራ በተራ እኩል በሆነ መጠን ካደባለቅን፣ ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን እናገኛለን፡፡

ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት የሚባሉ ሦስት ናቸዉ እነርሱም፡-

- ✓ ብርቱካናማ
- ✓ አረንጓዴ
- ✓ ወይነጠጅ



## የሁለተኛ ደረጃ ቀለማት አመሠራረት

ቀይ + ቢጫ = ብርቱካናማ

ቢጫ + ሰማያዊ = አረንጓዴ

ሠማያዊ + ቀይ = ወይነጠጅ



## ልምምድ 7

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች የጎደለውን ቀለም ሙሉ፡፡

1. ቀይ + ቢጫ = ________
2. ________ + ሰማያዊ = አረንጓዴ

3. __________ + ________ = ወይነጠጅ


## መልመጃ 1

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች በተጠየቃችሁት መሠረት መልስ ስጡ ፡፡

1. አንደኛ ደረጃ ቀለማት በቁጥር----------ናቸዉ፡፡
2. _________፣___________እና ቀይ ቀለም የአንደኛ ደረጃ ቀለማት ናቸው፡፡
3. የአንደኛ ደረጃ ቀለማትን እኩል በሆነ መጠን ተራበተራ ካደባለቅን ስንተኛ ደረጃ ቀለማት እናገኛለን ?
4. የሁለተኛ ደረጃ ቀለማት በቁጥር----------ናቸው፡፡
5. የሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ፃፍ፡፡

   ------------------------------------------------------------

6. ለሚከተሉት የቀለም ድብልቅ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡




## መልመጃ 2

በ ሀ ረደፍ ያሉትን የቀለማት ስም እና በ ለ ረደፍ ያሉትን የቁሳቁስ መልክ በማየት አዛምዱ፡፡

| ሀ | | ለ | |
|---|---|---|---|
| 1. | ቀይ | ሀ. |  |
| 2. | ሠማያዊ | ለ. |  |
| 3. | አረንጓዴ | ሐ. |  |
| 4. | ቢጫ | መ. |  |
| 5. | ብርቱካናማ | ሠ. |  |
| 6. | ወይነ ጠጅ | ረ. |  |

## መልመጃ 3

ከሚከተሉት የፍራፍሬ ሥዕል በማየት፣አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን የሚተኩ ወይም የሚያሳዩ ፊደሎችን በመለየት ፃፉ፡፡




ለምሳሌ፡

ሀ. ቀይ

ለ.-------------------

ሐ.-------------------


መ.------------------

ሠ.-------------------

ረ.--------------------

## ልምምድ 8

ከዚህ በታች በተቀመጠው ቅድም ተከተል መሠረት ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀቡ፡፡



## 2.3.2 ቀጥተኛ ህትመት

**ተግባር**

1. በእጃችሁ ላይ ቀለም፣ከሰል፣ጠመኔ፣አመድ፣ጭቃ እና የመሳሰሉት ነገሮችን በመቀባት ሌሎች ነገር ላይ አትማችሁት ታዉቃላችሁ? ወይም ሲያትሙ አይታችሁ ታዉቃላችሁ? አይታችሁ የሚታዉቁ ከሆነ እንዴት ዪታተማል?


ቀጥተኛ የህትመት ዘዴ የሰው ልጅ ከጥንት ዘመን ጀምሮ የተፈጥሮ ነገሮችን በመጠቀም ሲሰራ ነበር፡፡ ለምሳሌ፡- ቅጠል፣ አበባ፣ የእፅዋት ፍሬዎች እና የመሳሰሉት ነገሮች ወይም ቀለም በመንከር እና በመቀባት የተለያዩ ነገሮች ላይ በመጫን ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ቀጥተኛ ህትመት ከሌሎች የህትመት ዘዴዎች ቀላል ነው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ሰው በአከባቢው በሚገኙ ነገሮች በቀላል ሁኔታ መስራት ይችላል፡፡

ምሳሌ፡- የአንድ ቅጠል ቅርፅ ቀለም በመቀባት ዝርግ በሆነ ነገር ላይ ወደ ታች በመጫን መስራት ይቻላል፡፡

## ምሳሌ 1: የቅጠል ህትመት







## ምሳሌ 1: የእጅ መዳፍ ህትመት



## መልመጃ 4.

### የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

1. የቅጠል ህትመት ለማተም የሚያስፈልጉ ነገሮችን ፃፉ፡፡
2. የእጅ መዳፍ ህትመት ለማተም የሚያስፈልጉ ነገሮችን ፃፉ፡፡

## ልምምድ 9

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በተገለጹት የቅጠል ህትመት እና የእጅ መዳፍ ህትመት መሠረት በማድረግ በየግላችሁ ሥሩ፡፡

ሀ. የቅጠል ህትመት ሥሩ፡፡

ለ. የእጅ መዳፍ ህትመት ሥሩ፡፡

# 2.4. የድራማ ፣ቪድዮ እና ፎቶ መልዕክቶች

## የትያትር መልዕክት



★ ማስተላለፍ በፈለጋችሁት መልክት መሠረት አጭር ድራማ በመፍጠር ተለማመዱ፡፡

ድራማ ወይም ትያትር ሰውን በማዝናናት አጭር በሆነ መልክ የተለያዩ መልዕክቶችን ያስተላልፋል ፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን ባሕል እና ታሪክ ያስተዋውቃል፡፡ በድራማ ሰው ሀዘንን፣ ደስታን ፣ፍቅርን ፣አድናቆትን እና የመሳሰሉትን መግለፅ ይችላል፡፡ ትያትር በመድረክ ላይ ለተመልካቾች የሚቀርብ ነው፡፡

የግንዛቤ ጥያቄ 1

1. ድራማ ምን አይነት ነገር ሰውን ማስተማር ይችላል?

## የቪዲዮ መልዕክት



- ★ ለሕፃናት የተዘጋጁ ቪዲዮችን አይታችሁ ታዉቃላችሁ?
- ★ በተለያየ ቋንቋ ከተዘጋጁ የሕፃናት ቪዲዮች የቱን ትወዳላችሁ?





ቪዲዮ የምስል፣ተግባር እና ድምፅ ቅንጅት ሆኖ ፣ በቴሌቪዥን ወይም ሞባይል ላይ ማየት እና ማዳመጥ የምንችለው ነው፡፡


ስለዚህ በቴሌቪዥን ወይም ሞባይል ላይ በተግባር፣ምስል እና ድምፅ ተቀናጅተዉ የሚቀርብበት ሁኔታ **ቪዲዮ** ይባላል፡፡

ድራማ ፣ ትያትር እና ቪዲዮ የተለያዩ መልእክቶችን ያስተላልፋሉ፡፡ በተጨማሪም ለሕፃናት የሚዘጋጁ ፊደላትን ፣ ቁጥሮችን ፣ ስለ ንፅህና ለማስተማር እንዲሁም የተለያዩ አዝናኝ የሆኑ ጨዋታዎችን ቪዲዮዎችን በማዘጋጀት በተሌቪዥን ማቅረብ ይቻላል፡፡



**የግንዛቤ ጥያቄ 1**

1. ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ሥዕሎች ቪዲዮ አይታችሁ የሚታውቁ ከሆነ፣ እነ ማን ይባላሉ? ከእነርሱ ምን ተምህራችኋል?

2. ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች በየትኛው ቪዲዮ ውስጥ እንደተመለከታችሁ ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡




## የፎቶ መልእክት

በምዕራፍ አንድ ስለ ፎቶ በሰፊው ተምራችኋል፡፡ ድራማ፣ቪዲዮ እና ፎቶ መልዕክት ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡



ሰዎች በተለያዩ ሁኔታ ውስጥ ሆነው እና የተለያዩ ድርጊቶችን እየፈፀሙ እያሉ ፎቶ ቢነሱ፣ ፎቶው ሰዎቹ ያሉበትን ስሜት እና ምን እየሰሩ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ስለዚህ ፎቶ መልዕክት ማስተላለፍ ይችላል፡፡



*የሚተኛ ሕፃን ፎቶ*



*የሚትስቅ ሕፃን ፎቶ*

## የግንዛቤ ጥያቄ 2

1. የሚከተሉት  ፎቶዎች ምን አይነት ድርጊቶችን ያሳያሉ?




## የግንዛቤ ጥያቄ 3

2. የሚከተሉት  ፎቶዎች ምን  ያሳያሉ?






## መልመጃ 1

1. ፎቶ በምን አይነት ሁኔታ መልዕክት ያስተላልፋል?
2. የፎቶ እና ቪዲዮ ልዩነት ምንድነው?

# ምዕራፍ 3

# ባሕል እና ታሪክ

## 3. የባሕል ዕሴት መግለጫ

## 3.1 ባሕላዊ እና ዘመናዊ የሥነ-ጥበብ ሥራዎች

### 3.1.1 የባሕላዊ ሥነ-ጥበብ ሥራዎች

**ተግባር 1**

1. ስለ ኦሮሞ ህዝብ ባሕላዊ እና ዘመናዊ የእጅ ሙ-ያ ጥበብ የሚያውቁ አዛውንቶች/ ሽማግሌዎች በመጠየቅ፤ በክፍል ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

የእጅ ሙ-ያ ጥበብ ማለት፤ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሰዎች ባላቸው ችሎታ እና ብቃት በአከባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች የተለያዩ ነገሮችን መስራት ነው፡፡

ከእጅ ሞያ ስራ በተጨማሪ በአካባቢያችን የሚገኙ የተለያዩ እውቀቶችና ተጨባጭና ተጨባጭ ያልሆኑ ነገሮች ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተወራረሱ የመጡ ናቸው፡፡ እነርሱም የታሪክ ቅርስ ይባላሉ፡፡ የታሪክ ቅርሶቹም የሰውልጅ የፈጠራ ስራ ማሳያ ቅሪት የሆኑ እንደ የክብር እቃዎች የህንፃ ስራዎች የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የታሪክ ቅርሶች ማለት የሰው ልጅ የፈጠራ ሥራ ቁሳቁሶች፣ የተለያዩ ሙያዎች፣ሥነ-ሕንፃ ግንባታ እና ፍልስፍና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ እና የሕብረተሰብ ማንነት የሚገልፅ ነው፡፡

የኦሮሚያ ክልል ሕዝቡን የሚገልፁ በርካታ የባሕላዊ ስላጣኔ ቅርሶች አሏት፡፡ የእጅ ሙያ ጥበብ ለምሳሌ፡ የቤት ዕቃዎች፣ አልባሳት፣ የቤትአሠራር፣ ብረታ ብረት፣ የአምልኮ ሥፍራዎች፣ ቤተ-መዘክር ሙዚዬም እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የታሪክ ቅርሶች በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም -ተጨባጭ እና ተጨባጭ ያልሆኑ የታሪክ ቅርሶች በመባል ይጠራሉ፡፡

# ሰው ሰራሽ የታሪክ ቅርሶች

የታሪክ ቅርስ በሕዝቦች አኗኗር እና በሕብረተሰቡ የተሰሩ ሥራዎች ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ ነው፡፡ ይህም ዕሴቶች፣ ታሪካዊ የሆኑ ቦታዎች ፣ባህል ነክ ነገሮች እና ሌሎች በርካታ ነገሮችን ይይዛል፡፡ በዚህ ሁኔታ በሰው ልጅ ፈጠራ የተሰሩ ሥራዎች ፣ በርካታ መረጃ የያዙ ናቸው ፡፡

ሰው ሰራሽ የሆኑ የታሪክ ቅርሶች የሚከተሉት ናቸው፡፡እነርሱም፡-

- የቤተ-መንግስት ግንባታዎች
- መቃብር ላይ የተሰሩ ሃውልቶች
- ቤተ-እምነቶች
- ነገስታት እንደ መጠልያ ለመጠቀም ያሰሩት ስፍራዎች
- የሸክላ ሥራ
- የቆዳ ሥራ
- የሽመና ሥራ
- የስፌት ሥራ
- የእንጨት ሥራ
- የብረታ ብርት ሥራ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡ የአባ ጅፋር ቤተ-መንግስት ግንባታ፣ የኩምሳ ሞረዳ ቤተ-መንግስት፣ድሬ ሼክሁሴን የእምነት ሥፍራ፣ ጨለንቆ የኦሮሞ ጀግኖች የተሰውበት የውጊያ ስፍራዎች፣ ኮኮር፣አኖሌ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በአይን የማይታዩ እና በእጅ የማይዳሰሱ ቅርሶች የምንላቸው የገዳ ሥርዓት፣ አፈ-ታሪክ፣ ዕሴት፣ አስተምሮት፣ ኢሬቻ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

እነዚህ የታሪክ ቅርሶች አንድ ሀገር ወይም ሕብረተሰብ ያለውን ሀብት ያካትታል፡፡ በኦሮሚያ ከሚገኙ የተፈጥሮ ቅርሶች ዋሻዎች፣ ሀይቆች፣ተራራ፣ደን እና የመሳሰሉት መጥቀስ ይቻላል፡፡

የሰውን ልጅ ተግባር መሠረት በማድረግ፤ብዙ የታሪክ ቅርሶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህም ታሪክ፣ ስልጣኔ፣ እውቀት፣ ጀግንነት፣ ፍልስፍና፣ አስተምሮት፣ እምነት፣ የሕብረተሰቡ የአኗኗር ዘይቤ የሚያንፀባርቁ ሁሉንም አቅፎ በመያዝ ለአንድ ሀገር እድገት ከጥንት ዘመን ጀምረው እስከ አሁን ድረስ እንደ ታሪካዊ ቅርስ ትውልድ የሚማሩበት ነው፡፡

የጥንት ዘመን ጥበብ አሁን ላለው ጥበብ መሰረት ሲሆን ፤የተወሰነውን እንመልከት እነርሱም፡- የስፌት ሥራ፣ የሸክላ

ሥራ ፣የቆዳ ሥራ ፣የሽመና ፣የእንጨት ሥራ እና የብረታ ብረት ሥራ ናቸው፡፡

## 1. የስፌት ሥራ ጥበብ

**ተግባር**

1. በአከባቢያችሁ የሚሰሩ የእጅ ሥራ ሙያ ጥበባት ምንድናቸው?
2. ቤተሰብ ወይም ታላላቆቻችሁን በመጠየቅ ክፍል ውስጥ ተወያዩ፡፡

የስፌት ሥራ ከጥንት ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ከሚሠሩ ጥበባት አንዱ ነው፡፡ ይህ የጥበብ ሥራ የተለያዩ ነገሮች በመጠቀም የሚሰራ የስፌት ስራ ነው፡፡ ለስፌት ስራ ከምንጠቀምባቸው ነገሮች ውስጥ ስንደዶ፣ ሠርዶ፣ ዘንባባ፣ ቃጫ፣ ክር መጥቀስ ይቻላል፡፡

የሰው ልጅ ለዕለት ተዕለት ኑሮው ከሚጠቀምበት የሥፌት ሥራ ውጤቶች የወተት ማለቢያ፣ ሰፌድ፣ እንቅብ፣ ወንፊት፣ እርቦ፣ መሶብ፣ አገልግል፣ ሙዳይ እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ ፡፡ በአሁን ጊዜም ይህ የስፌት ጥበብ ስንደዶ እና ሰበዝን በተለያዩ ቀለማት ውስጥ በመንከር ፣ዲዛይን ወይም ስርዓተ ጥለት (ፓተርን) ይሰራል፡፡





የስፌት ሥራ ጥበብ ውጤቶች

## 2. የሸክላ ሥራ ጥበብ

የሸክላ ሥራ ጥበብ ከጥንት ጀምሮ እየተወራረሰ መጣና አሁንም ያለ የእጅ ሙያ ጥበብ ነው፡፡

ይህ ጥበብ በአከባቢያችን ከሚገኙ ነገሮች የሚሠራ ሲሆን ሕብረተሰቡ በቤት ውስጥ የሚጠቀሙበት ቁሳቁሶች እንደ ጋን፣ እንስራ፣ ስኒ፣ ማሰሮ፣ ጀበና፣ ምጣድ እና የመሳሰሉትን ያካትታል ፡፡

የእነዚህን ዕቃዎች ጥቅም ሲናይ፣ በድሮ ጊዜ በእንስራ ውሃ እየቀዱ፣ በጋን ጠጅ እና ጠላ እየጠመቁ፣ በእንስራ ቅቤ እያስቀመጡ፣ በምጣድ ደግሞ እንጀራ ሲጋግሩ እንደነበር ታሪክ ያረጋግጣል፡፡






## የሸክላ ሥራ ጥበብ ውጤቶች

# 3.የቆዳ ሥራ ጥበብ

የቆዳ ሥራ ጥበብ ከጥንት ዘመን ጥበባት አንዱ ሲሆን፤የሰው ልጅ ከተለያዩ እንስሳት ቆዳ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶችን ሲሰራ እንደነበረ ከታሪክ መዛግብት መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ዘመን በፍየል እና በበግ ቆዳ ላይ የተለያዩ ሥዕሎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

እንዲሁም የሰው ልጅ ከጥንት ዘመን ጀምሮ እንደ ጫጩ፣ ጋሻ፣ ቁርበት ፣መጫኛ፣ገመድ፣ቀበቶ፣ስልቻ፣አልጋ፣ኮሪቻ፣ ፉሎ እና የመሳሰሉትን ሲሰሩ ነበረ፡፡





## የቆዳ ሥራ ጥበብ  ዉጤቶች


## 4. ሽመና ሥራ ጥበብ



የሽመና ሥራ ጥበብ ከጥንት ጀምሮ ጥጥ በመፍተል ሲሰራ የነበረ እና በአሁኑ ጊዜ ትልቅ ቦታ የደረሰና በዘመናዊ መልክ ባህላዊ አልባሳት እየተሰራበት ያለ የእጅ ሞያ ጥበብ ነው ፡፡

ለምሳሌ ኩታ፣ ቡሉኮ እና የተለያዩ አልባሳት  በባሕላዊ እና ዘመናዊ መልክ እየተሰራ ይገኛል፡፡

## የሚከተሉትን ምሳሌዎችን ተመልከቱ፡፡



የሽመና ሥራ ጥበብ ውጤቶች

## 5. የእንጨት ሥራ ጥበብ

የእንጨት ሥራ ጥበብ በአሁን ጊዜ የሚያስደንቁ ነገሮች የሚሰሩበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከጥንት ዘመን ጀምሮ የነበረ ጥበብ ነው፡፡ በጥንት ዘመን የሰው ልጅ እንጨት በመጠረብ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ቁሳቁሶችን ሲሰራ ነበር፡፡ ከነዚህም የተወሰኑትን ለመጥቀስ አልጋ፣ በትር፣ በር፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ቆሪ ወይም ከእንጨት የሚሰራ ጎርጎድ ያለ ሰሃን፣ትራስ፣ሙቀጫ እና የተመሳሰሉት ናቸው፡፡





የእንጨት ሥራ ጥበብ ዉጤቶችን የሚያሳዩ ስዕሎች፡፡

## 6.የብረታ ብረት ሥራ ጥበብ





የብረታ ብረት ሥራ ጥበብ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ከሚሰሩ ሥራዎች አንዱ ሲሆን ፤ለሕብረተሰቡ ከፍተኛ ሚና ሲጫወት ቆይቷል፡፡ ለምሳሌ አንድ ገበሬ ምርቱን ለማምረት ማረሻ እና ወገል ያስፈልገዋል፡፡ ይሄንን ለማግኘት ደግሞ የብረታ ብረት ባለሙያ ያስፈልጋል፡፡ ከብረታ ብረት የሚሰሩ ነገሮች በርካታ ናቸው፡፡ እነርሱም፡- የአንገት ጌጥ፣ የእጅ ጌጥ፣ የጣት ቀለበት፣ እና መሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡





የብረታ ብረት ሥራ ጥበብ ውጤቶች

# መልመጃ 1

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሰው ሰራሽ ታሪካዊ ቅርስ ነው፡፡

   ሀ. የአባ ጅፋር ቤተ-መንግስት

   ለ. የሶፍ-ኡመር ዋሻ

   ሐ. የሃዋስ ወንዝ

   መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. ከሚከተሉት ምርጫዎች ውስጥ አንዱ በነቀምቴ ከተማ የሚገኝ ታሪካዊ ቅርስ ነው፡፡

   ሀ. ድሬ ሼክ ሁሴን

   ለ. የኩምሳ ሞረዳ ቤተ-መንግስት

   ሐ. የአባ ጅፋር ቤተ-መንግስት

   መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3. ከሸክላ አፈር በእጅ ሙያ ጥበብ የሚሰራ የቱ ነው?

   ሀ. እንስራ

   ለ. ምጣድ

   ሐ ጀበና

   መ.ሁሉም መልስ ናቸው

4. ከቆዳ የሚሰራ የእጅ ጥበብ ሥራ የቱ ነው?

   ሀ. ቁርበት

   ለ.ጫሬጩ

   ሐ.ስልቻ

   መ.ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

5. ከሽመና ሥራዎች የተለያዩ አልባሳት ይሰራሉ፡፡

ሀ.እውነት ለ.ሐሰት

6. ከስፌት ሥራ ውጤት የሚገኘው የቱ ነው?

ሀ. መሶብ ሐ. ሰፌድ

ለ. ወንፊት መ.ሁሉም መልስ ናቸው

7. ከእንጨት ሥራ ዉጤት የሚገኘዉ የቱ ነው?

ሀ. ጠረጴዛ ለ.ትራስ

ሐ. አልጋ መ.ሁሉም መልስ ናቸው

8. የብረታ ብረት ሥራ ጥበብ ልሆን የሚችል የቱ ነው?

ሀ. መረሻ ለ. መጥረብያ

ሐ. የአንገት እናየእጅ ጌጥ መ.ቢለዋ

ሠ.ሁሉም መልስ ናቸው

9. በአከባቢያችሁ የሚታወቁ የእጅ ሙያ ጥበብ ፃፉ፡፡

---------------------------------------

---------------------------------------

---------------------------------------

---------------------------------------

---------------------------------------

## 3.1.2 ዘመናዊ የሥነ-ጥበብ ስራዎች

ዘመናዊ ጥበብ ማለት በዚህ ዘመን ያሉት የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች ፍላጎታቸው እና አመለካከታቸውን የሚያንፀባርቁበት ነው፡፡ የጥንት ዘመን ጥበብ እንድንማር ያደረገን ፤በጊዜው የነበሩት የጥበብ ባለሙያዎች ሰርተው ለሕብረተሰቡ ያበረከቱት ጥበብ እንደሆነ ታሪክ ይናገራል፡፡ በጥንት ዘመን ከተሰሩት የጥበብ ሥራዎች የሸክላ ሥራ፣የሽመና ሥራ፣የቆዳ ሥራ፣የብረታ ብረት ሥራ፣የእንጨት ሥራ፣ቅርፃ ቅርፅ፣የቀለም ቅብ እና የተለያዩ ንድፎች አሁን ላለው ጥበብ ሙያ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

ይህ የጥንት ዘመን ጥበብ በማዘመን በአሁን ጊዜ ከቆዳ፣ከሸክላ እና ብረታ ብረት የተለያዩ ጌጣ ጌጦች በዘመናዊ መልክ እና ሰው በሚስብ ሁኔታ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ለምሳሌ፡ ከጥንታዊ የእጅ ሙያ ጥበቦች ውስጥ ከብረታ ብረት ስራ ማረሻን ወደ ትራክተር ከእንጨትና ቆዳ ስራዎች ደግሞ በርጩማ አልጋ የብረት በር በዘመናዊ መልክ እየተሰራ ይገኛል፡፡

.

## መልመጃ 2

1. ከብረት፣ ከቆዳና ከእንጨት የተሰሩ ዘመናዊ እቃዎችን ዘርዝሩ፡፡

## 3.2. የባሕላዊ እና ዘመናዊ ሙዚቃ ታሪክ

የአንድ ብሔር ባሕል በተለያዩ አቅጣጫ ቢገለፅም፤ባሕል የሚገለፅበት ዋነኛው መንገድ ሙዚቃ ነው፡፡ ሙዚቃ የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ነው፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ሙዚቃን ሲጠቀምበት የኖረና አሁንም እየተጠቀመበት አለ፡፡ ለምሳሌ በገዳ ሥርዓት የሚዘፈኑ ዘፈኖች እስከ ዛሬ ድረስ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የኦሮሞ ህዝብ ሙዚቃን ለተለያዩ ጉዳዮች በመጠቀም፤ባህሉን ከትውልድ ወደ ትልውድ ሲያሸጋግርበት ኖሯል፡፡

በታሪክ ውስጥ የኦሮሞ ህዝብ ሙዚቃን ለተለያዩ ጉዳዮች ይጠቀማሉ፡፡

ለምሳሌ፡-

- ደስታ እና ሃዘንን ለመግለፅ
- ፍቅርን ለመግለፅ
- በመማር እና ማስተማር ሂዴት

- ባህላቸዉን ለማንፀባረቅ
- በልማት ሥራዎች እንደ ማነቃቅያ
- ለሃገራችን ለመዘመር/ለመዝፈን
- ጀግኖችን ለማወደስ
- ለቤት እንስሳት መዘመር
- በገዳ ሥርዓት ውስጥ ለመጠቀም እና ወዘተ...

ያለፈው ሥርዓት የኦሮሞ ህዝብ ታሪክ እና ባሕል እንዳይታወቅ ከፍተኛ ጭቆና ያደረሰበት ቢሆንም፤ የኦሮሞ ህዝብ ባደረጉት ትግል ለውጥ ተገኝቷል ፡፡ በተለይ ድምፃውያን እና አንጋፋ ፀሐፊዎች ባደረጉት ተሳትፎ ፤በሕብረተሰቡ ዘንድ ተወዳጅነት ያገኙ እና የማይረሱ ናቸው፡፡

ለምሳሌ:-

ዶክተር አሊ ብራ　　　　　　　　　　አቢተዉ ከበደ





እልፍነሽ ቀኖ ሂካ ዋጂ



- ኑሆ ጎበና
- ዘርሁን ወዳጆ
- ሃሎ ዳዌ እና ወዘተ...ናቸዉ፡፡

የኦሮሞ ህዝብ ሙዚቃን በዘመናዊ መልክ ለተለያዩ ጉዳይ እየተጠቀሙበት መሆናቸው ይታወቃል፡፡

## ተግባር

1. በአከባቢያችሁ ሕብረተሰቡ ሙዚቃን ለምን አይነት ጉዳይ እንደሚጠቀሙ በመጠየቅ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

## 3.3. የቲያትር ከንውን እሴቶች መገለጫ

### የግንዛቤ ጥያቄ

ሀ. በአከባቢያችሁ የሚከናወኑ ዕሴቶች ታውቃላችሁ? ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡



የባሕል ዕሴቶች መገለጫ ሕብረተሰቡ በአኗኗራቸው ሁኔታ ማዕከል በማድረግ ሲተዳደሩበት የነበረው እና ዛሬም እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡

ይህ የባሕል እሴት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ሲሆን፣ ማንነታቸው እና የሕብረተሰቡን ቅርሶች የሚገልፅ ነው፡፡

የባሕል እሴት የተለያዩ ሕብረተሰብ ሥነ ጥበባትን ያካትታል፡፡

እነርሱም፡-

- ሙዚቃ
- ውዝዋዜ
- ትያትር
- ሥነ ጥበብ
- ምልክቶች
- ክብረ በዓላት
- የእጅ ጥበብ ሙያ
- ትረካ እና ወዘተ…ናቸው፡፡

ስለዚህ በቲያትር ክንዋኔ ውስጥ ሁሉንም ጥበባት በመጠቀም የሕብረተሰቡን ባሕል ዕሴቶችን ማሳየት ነው፡፡

## ባሕልን ለማስተዋወቅ የዕሴት ፋይዳ

ሀ. የሕብረተሰቡን ክህሎት ይጠብቃል፡፡

✓ ይህ የባህል እሴት፣ ቅርስ እንዲያድግ እና እንዲስፋፋ ያረጋል፡፡

ለ. የሰውን አዕምሮ ይቀርፃል፡፡

# የባሕል ዕሴቶች ባህርይ

የባሕል ዕሴቶች ባህርያት የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል፡፡

ለ.ትረካ እና በተግባር በማስመሰል፤የሕብረተሰቡን ባሕል እና ማንነት ይገልፃል፡፡

ሐ. የሕብረተሰቡን መስፋፋት ተከትሎ ያድጋል፡፡

ለዚህ ርዕስ የወሎ ህዝብ የባሕል ዕሴት ወጣት ወንድ እና ሴቶች የሚጫወቱት ባሕላዊ ጨዋታ **ጆቢዬ** በሚል ላይ የሚሰራ ይሆናል፡፡



የወሎ ኦሮሞ ባሕል እሴት የሚያሳይ ሥዕል፡፡

የጆቢዬ ጨዋታ በተለያዩ ሁኔታ ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡-በሰርግ ጊዜ፣ ከብት ሲጠብቁ፣ እንጨት ሲሰብሩ እና ወዘተ… ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ጨዋታ ወንዶች እና ልጃገረዶች አራቲ እና ሎሚ ይዘው ፣የባህል ልብስ በመልበስ፣ ዋሽንት ይዘው፣ ፊትለፊት በመቆም ዋሽንት ለሚጫተው ወጣት ግጥሙን እየነገሩ በዜማ እና በውዝዋዜ ይጫወታሉ፡፡

ወንዶች በአንድ በኩል ሴቶችም በሌላ በኩል በመቀመጥ፤ ዋሽንት ተጫዋቹን ተከትለው እንዲህ በማለት ጨዋታውን ይጀምራሉ፡፡

**ወንዶች** **ተቀባይ**

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ወንድ፡ ወይቲ ለጋ ቡቱ ዛዊያ ጆላኒ
ሀንድሌ ሲት ሆፉ ነቤኪ መላኒ

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ሴት :- ወይቲ ሎላ ዴምቱ ዝናር ኬ መርፋዱ
የሮ ነማ ብራ ነት ሙሙፋዱ
ወይቲ ቆፋ ቆፋ መሪ ነዱንገዱ

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ወንድ:- ከንጅቤ ሃ ጅቡ ሃቦኮኩ መሌ

አኒ ፋጤ ህንዲሱ ኤርጋ ረቢ መሌ

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ሴት:- ጎጆ ዱባ ገላ እት ገለን መና

ወል ብረቲ ኑ አርጌ ማልቱ ኑ አመና

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ወንድ: ወሊን ኦሉ ኬኛ ነምኒ ኑ ሀማታ

ጃለል ሃማዳ ዮም ከና ሶዳታ



**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ሴት: ጨፋ ዲደ ገርቢ

ኬሱማ ፈካዱ ሁላ ኬኛን ደርቢ

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ወንድ: ጨፋ ለጋ ገዲ ኢልሞ ሳላ ዲዳ

መነ ኬሰን ሴሂ አሴነ መስጂዳ

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ሴት: አኖ ሲን ጃለዳ ሲ ጂቤቲ ሚቲ

ሃማ አማ ቱሩን ኮ አዮ ሶዳዬቲ

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ወንድ: ኤርጋ አካስ ጀቴን ሸጌ ዱቢን ቶሌ

አስ ኮቱ ነቀቢ አን ኦፍ ወላሌ

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ሴት: ቢሻኒን ወራባ ኦኮሌ ለማኒ

ወል ፋደኔ በና ጎርዶመ ጃላኒ

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ወንድ: ጎጆ ግዱጋላ ቀራሩን ከበኒ

ስን ልቅምሳን ቱሬ ሲመሌ ህንቀበኒ

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ሴት: ጎጆ ግዱ ገላ ቀራሩን ከበኒ

አት ናልቅምሲ እሳን ዋን ደበኒ

## መልመጃ 1

### ከዚህ በታች ያሉትን በተጠየቃችሁት መሠረት መልሱ፡፡

1. የባሕላዊ ዕሴት ጥቅሞችን ጻፉ፡፡

2. የባሕላዊ ዕሴት ለሕብረተሰቡ ጥበብ ምን አይነት ጥቅም አለው?

ሀ.ሙዚቃ

ለ.ውዝዋዜ

ሐ.ጭውውት

መ.ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

3. የባህላዊ እሴት መገለጫ የሆነ የቱ ነው?

ሀ. ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል፡፡

ለ. በትረካ እና ተግባር በማስመሰል ይገለፃል፡፡

ሐ. የአንድ ሰው ታሪክ ብቻ ይዘከራል፡፡

መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው፡፡

## መልመጃ 2.

ጆቢዬ ከተሰኘው የወሎ ህዝብ ባሕል እሴት ጨዋታ ምን ተረዳችሁ?

# ምዕራፍ 4

## የሥነ ጥበባት መሥዕብ

## 4 የሥነ ጥበባት ሥራዎች አድናቆት

### 4.1 የስነ ጥበብ አድናቆት

ሥነ ጥበብ በሰው ልጅ አኗኗር ውስጥ ከፍተኛ ሚና እና ትስስር ያለዉ ነው፡፡ የሥነ ጥበብ አድናቆት በግድግዳ ላይ እና ቤተ-መዘክር (ሙዚዬም) ውስጥ ማስቀመጥ ከዚህ በፊት የተጀመረ ነው፡፡

የሥነ ጥበብ አድናቆት አስፈላጊነት በአይናችን በማየት፤በአከባቢያችን የሚገኙ የሥነ ጥባብት አሰራር እንዲንረዳ ይረዳናል፡፡ሥነ ጥበባት እንዲናደንቅ ከሚያደርጉን ነገሮች ውስጥ የተወሰኑን እንመልከት፡፡

- ✓ የሥነ-ጥበብ ዕዉቀት እና ግንዛቤ ለማካበት፡፡
- ✓ የሥነ-ጥበብ ዘዴዎች እና ለሥራ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በቃል እና በፅሑፍ የተቀመጠዉን በተግባር እንዲናሳይ ነው፡፡
- ✓ ባሕላዊ እና ዘመናዊ ሥነ-ጥበብ እንቅስቃሴዎች የመለየት ችሎታ ለማካበት እና እንዲናደንቅ ነው፡፡

የሥነ-ጥበብ  እድገት እና አዲናቆት ማዕከል ማድረግ ማለት ሰዎች እና ባሕል ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የሥነ ጥበብ ታሪክ ከዓለም ታሪክ ጋር የተያያዘ  ነው፡፡

ሥነ-ጥበብ  የሚንጠቀምበት መሣሪያዎች ፣የአድናቆት ዘዴ፣ትንታኔ እና የሕብረተሰቡ ግኑኝነት መነሻ በማድረግ የሰው ልጅ ዕለት ዕለት ኑሮ ለማሻሻል ተመራጭ መሳሪያ ነው፡፡ ስለዚህ ባሕልን ሳናዉቅ/ሳንረዳ ሥነ-ጥበብ ማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡

የሥነ-ጥበብ  አድናቆት የሚታይ ተጨባጭ ነገር ሳይሆን የግል ሃሳብ፣ዉስጣዊ ፍላጎት እና  ስሜት እንዲሁም የባሕል ተቀባይነት  ያለዉ ማሕበረሰባዊ ሁኔታ በተለያዩ ዲዛይን ላይ በመመሥረት ነው፡፡

የሥነ ጥበብ አድናቆት የሰዎችን ፍላጎት በመከተል፣የተለያዩ አመለካከቶች እንዲሁም የሥነ ጥበብ ትርጉም፣የሙሉ ልብ ንግግር እና ግንዛቤ በማስጨበጥ፤የሚሰማን ስሜት አጉልተዉ/ግልፅ አርጎ የሚያሳይ ነው፡፡

## 4.1.1 የሃገራችን ባሕልዊ ሥነ-ጥበብ ሥራዎች

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

1. የጥበብ ሥራ ምንድነው?

- ሥነ ጥበብ ማለት በሥነ ጥበብ ባለሙያ የተሰራ ሥራ ነው።
- የስነ ጥበብ ሥራ መረዳት የፈጠራ ችሎታን ያጎናፅፋል፡፡
- እነርሱም፡-በሥነ ጥበብ፣ፎቶ፣ቀለም ቅብ፣ግራፊክስ፣ቅርፃቅርፅ እና የመሳሰሉት መጠቀም ከጥንታዊ ሀሳብ በመነሳት ወደ ዘመናዊ ስነ -ልቦና የሚችሉት ላይ በመመሰረት ባሕል እና ታሪክ የሚገለጽበት ነው፡፡

ከ4ኛ እስከ 20ኛ ክፍለ ዘመን ያሉት የሃገራችን ሥነ-ጥበባት ለሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም የቤተ እምነት ባህላዊ ቀለም ቅብ እና የእጅ ሙያ ጥበብ ናቸዉ፡፡

በቤተ-እምነት ውስጥ የሚሰሩ ሥራዎች ሃይማኖትን የሚያንፀባርቁ ሥዕልና ፅሁፎች ሲሆን ፤የእጅ ጥበብ ሙያ የሚንላቸዉ ደግሞ የብረታ ብረት ፣ሸመና ፣ጅባ እና የተለያዩ ጌጣ ጌጥ ሥራዎች ነው፡፡

ከሥነ-ጥበባት ውስጥ አንዱ /ቪዥዋል አርት ሥነ-ስዕል ነው፡፡ ይህ በዐይን የሚታይ ነገር ደግሞ ፎቶ የማንሳት ጥበብ፣ቅርፃ ቅርፅ ፣ከነ ህንፃ ፣ቀለም ቅብ፣ሸክላ ሥራ ፣ብር እና ወርቅ ሥራ እና የቤት ውስጥ እቃዎች መሥራት ጥበብ መጥቀስ ይቻላል፡፡


ከቪዝዋል አርት የቀለም ቅብ፣ቅርፃ ቅርፅ እና ክነ-ሕንፃ ታዋቂ ነቸዉ፡፡ የሃገራችን ህዝቦች  ከጥንት ጊዜ ጀምረዉ ልዩ የሆኔ ከሃገራችን አኗኗር ሁኔታ ጋር የሚሄድ  የሥነ-ጥበብ እና የእጅ ሙያ ጥበብ አላቸዉ፡፡

ከጥንት ጊዜ ጀምረዉ በኦርቶዶክስ ቤተ እምነት ውስጥ የቀለም ቅብ ጥበብ በመሥራት፤ለሥነ-ጥበብ እድገት ከፍተኛ ሚና ተጫዉቷል፡፡ እንጨት በመጥረብ የፊት ጭንብል/ማስክ ፣ከእንጨት መስቀል መስራት እንዲሁም ሐረር አከባቢ የቤት ቁሳቁስ ሲሰሩ ቆይቷል፡፡


የሃገራችን የእጅ ሙያ ጥበብ ባሕል በዚህ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ከጅማት ክራር እየሰሩ፣ከሸንቦቆ ዋሽንት፣ከቀጭኔ ቆዳ ከበሮ፣ከቅል ወተት ማጠራቀሚያ ፣ከቃጫ ጅባ፣ከጥጥ ልብስ፣ከሥንደዶ ስፌትን፣ከዘንባባ ሳሌን ና የመሳሰሉትን ሲሰሩ ነበር፡፡



ከሥንደዶ፣ቆዳ እና ዶቃ የተሰሩ የእጅ ሙያ ጥበብ የሚያሳይ ስዕል፡፡




ከሥንደዶ፣ቆዳ ፣እንጨት፣እና ጨሌ የተሰሩ የእጅ ሙ.ያ ጥበብ
የሚያሳይ ስዕል፡፡



**የተለያዩ ጌጣ ጌጥ ከጨሌ እና ብረታ ብረት የተሰሩ የእጅ ሙያ ጥበብ፡፡**



ከሸክላ የተሰሩ የእጅ ሙያ ጥበብ፡ የሚያሳይ ሥዕል፡፡



ከእንጨት፣ቆዳ እና ሥንደዶ የተሰሩ የእጅ ሙያ ጥበብ የሚያሳይ ስዕል፡፡

## 4.2 የባሕላዊ ሙዚቃ አድናቆት

ተግባር

1. የአከባቢያችሁን ባህላዊ ሙዚቃ ፃፉ፡፡
2. ከአከባቢያችሁ ባህላዊ ሙዚቃ ውስጥ በጣም ታዋቂ ሆኑትን በመለማመድ ለክፍል ተማሪዎች አቅረቡ፡፡
3. ከቀረቡት ባህላዊ ሙዚቃ ውስጥ የሚትወዱት እና የሚታደንቁት እንደ ደረጃቸዉ በቡድን ግለፁ፡፡

## ጫወታ በትያትር

በተለያዩ ትምህርት እንደተማራችሁት፤የኦሮሞ ህዝብ አኗኗር በሥነ-ጥበብ የተሞላ ነው፡፡ የተለያዩ ክንዉኖች ጥበባዊ በሆነ መልክ መግለፅ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ፤ጀግናን ሲያሞግሱ፤ፈሪዉን ሲያጥላሉ፤ሃገራቸዉን ሲጠብቁ፤ከብቶቻቸዉን ሲጠብቁ እና ሲጋቡ ጥበባዊ በሆነ መልክ መልዕክቱን ያስተላልፋል፡፡ የኦሮሞ ሥነ-ጥበባዊ ክንዉን ጌራርሳ ውይም ሽለላ አንዱ ነው፡፡

## የልምምድ ጥያቄዎች

1. ስለ ጌራርሳ/ሽለላ ሰምታችሁ የሚታዉቁ ነገር ለክፍል ተማሪዎች ግለፁ፡፡
2. የሚሽልል ሰው አይታችሁ የሚታዉቁ ከሆነ፤ምን አይነት ተግባር ያሳያሉ? ለምን ይሽልላሉ?
3. የሚሽልል ሰው ምን ይይዛል?
4. ይህ ሽለላ አስደንቋል/ቆሻል ወይ ?

# በሽለላ ጫወታ ጀግኖችን ማወደስ



ተማሪዎች የወሎ ባሕላዊ ልብስ ለብሰው፣ሚዶዉን ሰክተዉ፣መፋቅያ ይዘዉ፣በዝናር ወገባቸዉን ታጥቀዉ፣ዱላ ይዘዉ ይጫወታል፡፡



በመጀመርያ አንድ ተማሪ ብቻዉን ተቀምመዉ በሃሳብ እያጉረመረመ ፤ ከጓደኞቹ ፊትለፊት ሁለት ለሁለት ይገባሉ፡፡

1ኛ ሴት ተማሪ: ማል ታቴ ያዶፍታ?

1ኛ ወንድ ተማሪ : ጎቶታ ኬኛ ያዴ

2ኛ ሴት ተማሪ: ዋሎ ጀቹን ዋሎ

ኑህ ሲፍ ጅራ ህን ያዳእን ማሎ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ…ሃ….

1ኛ ወንድ ተማሪ :  ናን ያዳዴ ማሌ ታካ ህን ያዶፍኔ

ዋሎ ታኡ ኬኛ አን ህን እራንፋኔ

ያዶ እሼ ህን ቃብኑ ጃግና እራ ዳላኔ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ...ሃ....

1ኛ ወንድ ተማሪ፡ እልማን ሃሳን አሜ

ዳዌ እራ ራቅሜ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ...ሃ....

2ኛ ወንድ ተማሪ: እጆሌን ዋዳይ፣ዋዳይ ባቦ ጃራ

ጂሌራ ማንዲሂ ዲና አሪኤ ኦፍ እራ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ...ሃ....

3 ኛ ወንድ ተማሪ : ካን ኡስማን ጥዬ ፊ ካን ኡማር ቡሹራ

ሳባር ሳካ ጀቻ ፉላሃን ዋዩራ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ...ሃ....

1ኛ ወንድ ተማሪ : ካን እማም ዩሱፍ

ጋርፉራን ዱፉፍ

ዲና ሆንጌሱፍ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ...ሃ....

1ኛ ሴት ተማሪ : እንስካን ዋርቅቱ

ዱካና ኬ እፍቱ

ጢቂን ናት ህን ሃፍቱ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ…ሃ….

1ኛ ወንድ ተማሪ : ኮርም ጋፋ ሎሌ

ሁሉም ተማሪዎች: ሃ..ሃ…ሃይ ኮርማን ጋፎ

1ኛ ወንድ ተማሪ: እንጂፋኖን ጋሌ

ሁሉም ተማሪዎች:ሃ..ሃ…ሃይ ኮርማን ጋፎ

## መልመጃ 1

### አጭር መልስ መልሱ

1. በዚህ ጌራርሳ/ሽለላ የተገለፁትን ጀግኖች ስም ዝርዝር ፃፉ::
2. በዚህ ጌራርሳ/ሽለላ ውስጥ ከየትኛ ጎሳ ነው የፈለቁት?

# ምዕራፍ 5

# የስነ ጥበባት ትስስር

## 5.1 የስነ-ጥበባት ግኑኝነት


### ተግባር

ስለ ቀለማት የሚያሳይ የመዝሙር ክሊፕ ታደሙ፤በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደ ተዘመሬ መሆኑን ያሳየናል፡፡ በተጨማሪም የሥነ-ጥበባት ግኙንኘት ከዚህ መዝሙር መረዳት እንደሚቻል ተነጋገሩ፡፡



# ቀለም ምንድነው?

## ቀለም የአንድን ነገር መልክ ነው፡፡ እነርሱም:



ሰማያዊ

ቀይ

ነጭ

ቢጫማ አረንጓዴ

አረንጓዴ

ሮዝ

ጥቁር

ዉሃ ሠማያዊ

ቡራቡሬ

ዳላቻ

ብርማ

አረንጓዴ

ቡኒ

ወርቅማ

ቢጫ አረንጓዴ

ወይነ ጠጅ

## 5.2 ሌሎች ትምህርቶችን መማር ውስጥ ያለዉ የሥነ-ጥበባት ጥቅሞች

### 5.2.1.ሌሎች ትምህርቶችን መማር ውስጥ ያለዉ የሙዚቃ አስፈላጊነት

#### የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. በመዝሙር ምን አይነት ትምህርት ተምራችሁ ታዉቃላችሁ?
2. የተለያዩ ትምህርት የተማራችሁበት ሦስት (3) መዝሙሮችን ፅፋችሁ በቡድን በመለማመድ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡
3. ሌሎች ትምህርት ማስተማር ውስጥ ያለዉ የሥነ ጥበብ ድርሻ እና ጥቅሞችን ተወያዩ፡፡ የተወያያችሁበትን ነገር ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

### ማጠቃለያ ሓሳብ

ሕፃናት በጫወታ እና ጥበባዊ በሆኔ መልክ ከተማሩ፤በአጭር ጊዜ ውስጥ በማይረሳ ሁኔታ ትምህርት መያዝ ይችላሉ፡፡ የትምህርት ይዘትን ወደ መዝሙር በመቀየር ማስተማር፤ትምህርቱ ዉጤታማ እንዲሆን ይረዳል፡፡

## 5.2.2 ሌሎች ትምህርት ማስተማር ውስጥ ያለዉ ድርሻ

### የስሜት ህዋሳት






**የሰው ልጅ አምስት (5) የስሜት ህዋሳት አሉት፡፡**




**እነዚህ አካላት አንድ ቀን ተጣልተዉ፤በጣም ተከራከሩ፡፡ ሁላቸዉም እንደሚከተለዉ ተራ በተራ በማካበድ እራሳቸዉን ገለፁ፡፡**


እኔ ባላይላችሁ ኖሮ፤ማየት
አትችሉም ነበር።


አንተ ተዉ…ወደ እናንተ የሚመጣ ክፉ እና
መልካም ድምጽ ባልለይ ኖሮ፤እንዴት ትሆኑ ነበር።


እናንተ ለምን ትጣላላችሁ፤ እኔን የሚጋጭ
ነገር ባልጠብቅ ኖሮ፤ መኖራችሁ ከባድ ነበር።




## መልመጃ 1

1. ከዚህ ጭውውት ምን ተረዳችሁ?

ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014/2022

# ሥነ - ጥበባት ትምህርት

## የተማሪዎች መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል

ዋጋ ________________